የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ስምንተኛ ዓመት ቁጥር ፵፬
አዲስ አበባ ሐምሌ ፰ ቀን ፪ሺ፲፬ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

28th Year No. 44
ADDIS ABABA 15th July, 2022

**ማውጫ**

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፸፬/፪ሺ፲፬
የመንገድ ትራንስፖርት አዋጅ……….ገጽ ፲፬ሺ፫፻፸፩

**Content**

Proclamation No. 1274/2022
Road Transport Proclamation…...Page 14371

## አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፸፬/፪ሺ፲፬

## የመንገድ ትራንስፖርት አዋጅ

ለሀገራችን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ዕድገት የመንገድ ትራንስፖርት አገልግሎት የሚያበረክተውን አስተዋጽኦ የበለጠ ለማጎልበት ዘርፉ አስተማማኝ፤ የተቀናጀ፤ ዘመናዊና ደኅንነቱ የተረጋገጠ ሆኖ እንዲራመድ ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ፣

የመንገድ ትራንስፖርት አስተዳደር የመንግሥትን የኢኮኖሚና ማህበራዊ ጉዳዮች ፖሊሲ በአግባቡ ለመተግበር፤ የመንገድ ትራስፖርት እስከታችኛው የሀገራችን መዋቅር ድረስ ጠንካራ አፈጻጸምና የቁጥጥር ሥርዓት እንዲኖር ለማድረግና የመንገድ ትራስፖርት ዘርፉን በቴክኖሎጂ ተደግፎ ተደራሽና አስተማማኝ እንዲሆን ለማድረግ የሚያስችል ሥልጣንና ተግባር ማበጀት በማስፈለጉ፣

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## PROCLAMATION NO.1274/2022

## ROAD TRANSPORT PROCLAMATION

**WHEREAS**, the economic and social development of the country requires that road transport service be regulated to make it more reliable, integrated, modern and safe;

**WHEREAS**, it is necessary to ensure that the administration of road transport properly implements the government’s economic and social affairs policies; ensure that there is a strong enforcement and monitoring system in the road transport up to the lower administrative level; and ensure that the road transport sector is equipped with technologies essential for its reliability and accessibility;

**NOW, THERFORE,** in accordance with Article 55(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ “የመንገድ ትራንስፖርት አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፸፬/፪ሺ፲፬” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### ፪. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

፩/ **“ሚኒስቴር”** ወይም **“ሚኒስትር”** ማለት እንደ ቅደም ተከተሉ የትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፤

፪/ **“ድርጅት”** ማለት በንግድ የመንገድ ትራንስፖርት አገልግሎት ሥራ ላይ ለመሰማራት በኢትዮጵያ የንግድ ሕግ መሠረት የተቋቋመ እና በዚህ አዋጅ መሠረት የተመዘገበ የሕግ ሰውነት ያለው አካል ነው፤

፫/ **“ተቋም“** ማለት በትራንስፖርት ዘርፍ የተሰማራ እና በዚህ አዋጅ፣ በአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ አዋጅ፤ በተሽከርካሪ መለያ፣ መመርመሪያና መመዝገቢያ አዋጅ እና በጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች ዲመሬጅ ክፍያ አዋጅ መሠረት ቁጥጥር እና ክትትል የሚደረግበት መንግሥታዊ የሆነ ወይም መንግሥታዊ ያልሆነ ተቋም ነው፤

፬/ **“የመንገድ ትራንስፖርት”** ማለት ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም በተለያየ የትራንስፖርት ዘዴ በመንገድ ላይ ሰዎችን ወይም ዕቃን ወይም ሰዎችን እና ዕቃን ከአንድ ስፍራ ወደሌላ

## PART ONE

## GENERAL PROVISIONS

### 1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "Road Transport Proclamation No. 1274/2022".

### 2. Definition

In this Proclamation, unless the context requires otherwise:

1/ "**Minster**" or "**Ministry**" means the Minister or Ministry of Transport and Logistics, respectively;

2/ "**Enterprise**" means a legal person engaged in commercial road transport service as established in accordance with the Ethiopian Commercial Code and registered in accordance with this Proclamation.

3/ "**Institution**" means any governmental or non-governmental institution engaged in the transport sector; and regulated and administered by this Proclamation, the Driver’s Qualification Certification License Proclamation and the Vehicles Identification, Inspection and Registration Proclamation and Trucks Demurrage Proclamtion.

4/ “**Road Transport**” means for the purpose of this Proclamation the service of transporting persons or goods or persons and goods from point of

ስፍራ የማጓጓዝ አገልግሎት ሲሆን የባቡር ትራንስፖርትን አይጨምርም፤

፭/ **“የመንገድ ትራንስፖርት አገልግሎት”** ማለት በግለሰብ ወይም በድርጅት የሚከናወንና መንገደኞችን ወይም ዕቃዎችን በክፍያ የማጓጓዝ የንግድ ሥራ ሆኖ እንደሚከተለው የግል ወይም የንግድ የመንገድ ትራንስፖርት ተብሎ ተለይቷል፡-

ሀ) **“የግል ንግድ የመንገድ ትራንስፖርት”** ማለት መንገደኞችን ወይም ዕቃዎችን የሚያመላልሰው ተሽከርካሪ ንብረትነቱ የድርጅት ሆኖ፤

(1) የሚመላለሱት ዕቃዎች የዚያው ድርጅት ንብረት የሆኑ ወይም ለጥገና ወይም ለማደስ በአደራ የተሰጡ የሆኑ እንደሆነና ዕቃዎችን ማመላለስ ለድርጅቱ ዓይነተኛ የንግድ ሥራ አስፈላጊና ማሟያ የሆነ እንደሆነ፤

(2) የሚመላለሱት መንገደኞች የዚያው ድርጅት ሠራተኞች ሆነው የሚመላለሱትም ወደ ሥራ ቦታቸውና ከሥራ ቦታቸው የሆነ ወይም የድርጅቱን ሥራ ለማከናወን የሆነ እንደሆነ ነው፤

departure to point of destination using different modes of road transport in exclusion of railway transport;

5/ "**Road Transport Service**" means the service of transporting of passengers or goods with remuneration by natural or juridical persons; and is classified as either private or commercial road transport as follows:

a) "**Private Commercial Road Transport**" means if the vehicle used for carrying passengers or goods is owned by the enterprise, and

(i) in the case of goods being transported, the goods are owned by the enterprise or have been entrusted to it for the purpose of maintenance or repair and the transportation of said goods is necessary and complementary to the principal commercial activity carried out by the enterprise;

(ii) in the case of passengers being transported, the passengers are employees of the enterprise and are being transported to or from their place of work or are engaged in the business of the enterprise;

ለ) **"የንግድ የመንገድ ትራንስፖርት"** ማለት ከከተማ ታክሲ በስተቀር የግል ተብሎ ያልተመደበ ማንኛውም የንግድ የመንገድ ትራንስፖርት አገልግሎት ነው፤

፮/ **"የንግድ ማህበር"** ማለት ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም አግባብነት ባላቸው የኢትዮጵያ የንግድ ሕጎች መሠረት የንግድ ሥራ ለማከናወን ሥልጣን ባለው አካል የተመዘገበና የትራንስፖርት ንግድ ሥራ እንዲያከናውን የሚያስችለው የንግድ ፈቃድ የተሰጠው ግለሰብ ወይም ድርጅት ነው፤

፯/ **"የዲስፕሊን መመሪያ"** ማለት በሚኒስቴሩ የወጣ የዲስፕሊን እርምጃ አወሳሰንና አፈፃፀም መመሪያ ነው፤

፰/ **"አውራ ጎዳና"** ማለት የኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር የሚያስተዳድረውና አውራ ጎዳና ብሎ የሚሰይመው መንገድ ነው፤

፱/ **"የስምሪት ፕሮግራም"** ማለት የሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎችን የዓመት፣ የወር፣ የሳምንት ወይም የቀን አገልግሎትና እንቅስቃሴ የሚወስን የስምሪት መርሃ-ግብር ነው፤

፲/ **"የመንገድ ተጠቃሚ"** ማለት አሽከርካሪ፣ የብስክሌት አሽከርካሪ ወይም የመንገድ ትራንስፖርት ተገልጋይ ሲሆን እግረኛን ይጨምራል፤

፲፩/ **"አሽከርካሪ"** ማለት አግባብነት ባለው የመንገድ ትራንስፖርት ሕግ መሠረት ተሽከርካሪን እንዲያሽከረክር በሕግ ሥልጣን ከተሰጠው አካል የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ የተሰጠው የተፈጥሮ ሰው ነው፤

b) "**General Commercial Road Transport**" means except the city taxi all commercial road transport not classified as private;

6/ "**Business Entity**" means for the purpose of this Proclamation any person or enterprise registered as trader in accordance with the applicable commercials laws of Ethiopia and is issued with a transport trade license from the competent authority;

7/ "**Disciplinary Manual**" means a Directive issued by the Ministry governing disciplinary action and its execution;

8/ "**Highway**" means a road administered and designated as such by the Ethiopian Roads Administration;

9/ "**Trip Schedule**" means yearly, monthly, weekly or daily program scheduled for the operation of public commercial road transport vehicles;

10/"**Road User**" means a driver, bicycle rider and a person using a road transport service; and includes pedestrian;

11/"**Driver**" means a natural person issued with a valid driving permit from a competent authority for operating a vehicle in accordance with the appropriate road transport law;

፲፪/ **"የስምሪት መስመር"** ማለት በሚኒስቴሩ የሚወሰን የሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪ የስምሪት መነሻና መድረሻ ነው፤

፲፫/ **"መንገደኛ"** ማለት በተሽከርካሪ ተሳፍሮ የሚሄድ ማንኛውም ሰው ሲሆን አሽከርካሪውን፣ ገንዘብ ተቀባዩንና በተሽከርካሪው ላይ የተመደበ ማንኛውንም ሌላ ሠራተኛን አይጨምርም፤

፲፬/ **"ቁጥጥር"** ማለት በዚህ አዋጅ፣ በአዋጁ መሠረት የሚወጡ ደንቦች፣ መመሪያዎች፣ ደረጃዎች እና ውሳኔዎች በትክክል በሥራ ላይ መዋላቸውን የማረጋገጥ ተግባር ነው፤

፲፭/ **"ተቆጣጣሪ"** ማለት የቁጥጥር ተግባሮችን እንዲያከናውን በማናቸውም የኢትዮጵያ ክፍል በሚኒስቴሩ የሚመደብ ሠራተኛ ነው፤

፲፮/ **"መንገድ"** ማለት በተለምዶ ተሽከርካሪዎች የሚጠቀሙበት ማንኛውም መንገድ፣ የከተማ መንገድ፣ አውራ ጎዳና ወይም መተላለፊያ ሲሆን ድልድይንም ይጨምራል፤

፲፯/ **"ተሽከርካሪ"** ማለት ልዩ ወታደራዊ ተሽከርካሪዎችን ሳይጨምር በመንገድ ላይ በመንኮራኩር የሚሄድ ማንኛውም ዓይነት ተሽከርካሪ ሆኖ ሠረገላን፣ ሳይክልን፣ ባለሞተር ተሽከርካሪን፣ ግማሽ ተሳቢን እና ተሳቢን ያጠቃልላል፤

12/ "**Assigned Route**" means the specific departure and destination point to be determined by the Ministry where public commercial road transport vehicles are assigned to operate;

13/"**Passenger**" means any person boarding for travel in a vehicle, other than the driver, cashier or any other person assigned to work on a vehicle;

14/"**Supervision**" means ascertaining of the proper implementation of Road Transport Proclamation; Regulations, Directives, Standards and decisions issued in accordance with this Proclamation;

15/"**Supervisor**" means an employee assigned by the Ministry to execute supervisory activities in any part of Ethiopia.

16/"**Road**" means any road, street, highway or other travel route customarily used by vehicles including bridges;

17/"**Vehicle**" means any type of wheeled vehicle other than specialized military vehicle; and includes wagons, cycles, motorized vehicles, semi-trailers and trailers;

፲፰/ **"ሠረገላ"** ማለት ከብስክሌት፣ ከባለሞተር ተሽከርካሪ፣ ከግማሽ ተሳቢ እና ከተሳቢ በስተቀር ማንኛውም ተሽከርካሪ ነው፤

፲፱/ **"ብስክሌት"** ማለት በሚያሽከረክረው ሰው የጡንቻ ኃይል አማካኝነት እየተነዳ የሚሄድ ባለሁለት እግር ተሽከርካሪ ሲሆን ለመንቀሳቀስ ተጨማሪ ወይም አማራጭ የኤሌክትሪክ ኃይልን የሚጠቀም ባለሁለት እግር ተሽከርካሪን ይጨምራል፤

፳/ **"ባለሞተር ተሽከርካሪ"** ማለት በመካኒካል ወይም በኤሌክትሪክ ኃይል እየተንቀሳቀሰ የሚሄድ ተሽከርካሪ ሆኖ የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪ፣ ባለሞተር ብስክሌት፣ የግል አውቶሞቢል፣ የሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪ፣ ጎታች መኪና እና ልዩ ተንቀሳቃሽ መሣሪያን ያጠቃልላል፤

፳፩/ **"የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪ"** ማለት ማንኛውንም ዓይነት ዕቃ እንዲያመላልስ ተብሎ የተሠራና ለዚሁ አገልግሎት እንዲውል የተደረገ ባለሞተር ተሽከርካሪ ሲሆን ጎታች መኪናን ይጨምራል፤

፳፪/ **"ባለሞተር ብስክሌት"** ማለት የጎን ተሽከርካሪውን ሳይጨምር ክብደቱ ከ፬፻ ኪሎ ግራም የማይበልጥ ፬(ከአራት) መንኮራኩር በታች ያለው ባለሞተር ተሽከርካሪ ነው፤

፳፫/ **"የግል ተሽከርካሪ"** ማለት ከጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪ፣ ከባለሞተር ብስክሌት፣ ከሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪ፣ ከጎታች መኪና እና ከልዩ ተንቀሳቃሽ መሣሪያ የተለየ ለግል መጠቀሚያ የሚውል ባለሞተር ተሽከርካሪ ነው፤

18/"**Wagon**" means any vehicle other than a bicycle, a motorized vehicle, a semi-trailer or a trailer;

19/"**Cycle**" means a pedaled vehicle with two wheels in tandem as propelled by the muscular force of the person riding it; and includes bicycles using electricity as power source;

20/"**Motor Vehicle**" means a vehicle moving by mechanical or electrical power; and is classified as truck, motorcycle, private motor car, public service vehicle, truck tractor and special mobile equipment;

21/"**Truck**" means a motor vehicle made or adapted for the conveyance of goods or used primarily for the conveyance of goods of any description; and includes a truck tractor;

22/"**Motorcycle**" means a motor vehicle with less than 4 (four) wheels, the weight of which, exclusive of any side-car attached thereto, does not, when unladed, exceed 400 kilograms;

23/"**Private Vehicle**" means a motor vehicle used for private service exclusive of a truck, a motorcycle, a public service vehicle, a truck tractor and special mobile equipment;

፳፬/ **"የሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪ"** ማለት መንገደኞችን ለማመላለስ የሚያገለግል ባለሞተር ተሽከርካሪ ሲሆን የንግድ አውቶሞቢልና አውቶቡስን ያጠቃልላል፤

፳፭/ **"የንግድ አውቶሞቢል"** ማለት ከአስራ ሁለት የማይበልጡ መንገደኞችን ለማመላለስ የሚችል የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ማመላለሻ ተሽከርካሪ ነው፤

፳፮/ **"አውቶቡስ"** ማለት የታክሲ አገልግሎት ከሚሰጡት በስተቀር ከአስራ ሁለት መንገደኞች በላይ ለማመላለስ የሚችል የሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪ ነው፤

፳፯/ **"ጎታች መኪና"** ማለት በተለይ ሌሎች ተሽከርካሪዎችን ለመጎተት የሚያገለግል ሆኖ የሌላ ጭነትን ሳይሆን የሚጎትተውን ተሽከርካሪና በተጎታቹ ላይ ያለውን ጭነት ክብደት ብቻ በከፊል ለመሸከም የተሠራ ባለሞተር ተሽከርካሪ ነው፤

፳፰/ **"ልዩ ተንቀሳቃሽ መሣሪያ"** ማለት ሰውን ወይም ዕቃን በመንገድ ላይ እንዲያመላልስ ሆኖ የተሠራ ተሽከርካሪ ሳይሆን ለእርሻ፣ ለአትክልት፣ ለከብት እርባታ፣ ለመንገድ፣ ለሕንፃ፣ ለቁፋሮ ወይም ለማንኛውም ተመሳሳይ ሌላ ሥራ የተሠራ ወይም ለዚሁ ጉዳይ እንዲውል የተደረገ ባለሞተር ተሽከርካሪ ነው፤

24/"**Public Transport Vehicle**" means a motor vehicle used to carry passengers; and includes commercial motor car and motor omnibus;

25/"**Commercial Motor Car**" means a public transport service vehicle having accommodation for not more than twelve passengers;

26/"**Motor Omnibus**" means a public service vehicle other than vehicles engaged in taxi service; and having a seat accommodation for more than twelve passengers;

27/"**Truck Tractor**" means a motor vehicle made or adapted for drawing other vehicles, and so constructed as to carry no load other than part of the weight of the vehicle and the load thereon;

28/"**Special Mobile Equipment**" means any motor vehicle designed, made, adapted or used for agricultural, horticultural, livestock, road construction, building, digging or any other similar purposes in exclusion of vehicles designed, adapted or used for the transportation of persons or goods;

፳፱/ **"ግማሽ ተሳቢ"** ማለት ለመንገደኞች ወይም ለጭነት ማመላለሻ የሚያገለግልና በሌላ ባለሞተር ተሽከርካሪ የሚሳብ ሆኖ የተሽከርካሪውም የጭነቱም ክብደት በከፊል በባለሞተር ተሽከርካሪው ላይ እንዲያርፍ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ እንዲሳብ ተደርጎ የተሠራ ተሽከርካሪ ነው፤

፴/ **"ሙሉ ተሳቢ"** ማለት ለራሱ የተለየ የሞተር ኃይል የሌለው ሆኖ ጎታች በሆነ በሌላ ባለሞተር ተሽከርካሪ ላይ ሊቀጠልና ሊጎተት የሚችልና ክብደቱ ጎታች በሆነው ባለሞተር ተሽከርካሪ ላይ እንደማያርፍ ሆኖ የተሠራ ተሽከርካሪ ነው፤ ሆኖም ከባለሞተር ብስክሌት ጋር ተያይዞ የሚሳበውን የጎን ተሽከርካሪ አይጨምርም፤

፴፩/ **"ሞተር አልባ የትራንስፖርት መገልገያ"** ማለት በመካኒካል ወይም በኤሌክትሪክ ኃይል እየተንቀሳቀሱ ከሚሄዱ ተሽከርካሪዎች በስተቀር ማናቸውም ሞተር አልባ የሆነ የትራንስፖርት መገልገያ መሣሪያ ነው፤

፴፪/ **"የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት መናኸሪያ"** ማለት የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ተሽከርካሪዎች መንገደኞችን እንዲያሳፍሩ እና እንዲያደርሱ ወይም የመንገደኞች ዕቃዎችን እንዲጭኑበት/ እንዲያራግፉበት ታስቦ የለማ መሠረተ-ልማት ነው፤

፴፫/ **"የአውቶቡስ ዴፖ"** ማለት የህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ሰጪ አውቶቡሶች ለጥገና፣ ለመታጠቢያ፣ ነዳጅ ለመቅዳት እና ለማደር በጋራ እንዲጠቀሙበት ታስቦ የለማ መሠረተ-ልማት ነው፤

29/"**Semi-Trailer**" means a vehicle designed or adapted for carrying passengers or goods; and so constructed as to be drawn by a motor vehicle that some part of its weight and the load thereon rest upon or is carried by the motor vehicle;

30/"**Trailer**" means a non-motorized vehicle designed to be pulled by and behind a motor vehicle; and so constructed that no part of its weight rests upon the motor vehicle by which it is drawn, but shall not include a side car attached to a motorcycle;

31/"**Non-motorized Transport Equipment**" means any non-motorized equipment used for transport services except motor vehicles operated with mechanical or electrical force;

32/ "**Public Transport Station**" means infrastructure developed and designated for the boarding and disembarkation by public transport vehicles of passengers or loading/unloading of their cargos;

33/ "**Bus Depot**" means a hub infrastructure designated for maintenance, car-wash, fueling and parking of Omnibuses;

፴፬/ "**የጭነት ትራንስፖርት አገልግሎት መናኸሪያ**" ማለት የጭነት ትራንስፖርት አገልግሎት ሰጪዎች ተሽከርካሪዎች ጭነቶችን እንዲጭኑበት፣ እንዲያራግፉበት፣ እንዲያሽጉበት እና እንዲበትኑበት ታስቦ የለማ መሠረተ-ልማት ማለት ነው፤

፴፭/ "**መጋዘን**" ማለት የጭነት ትራንስፖርት አገልግሎት መነሻ ወይም መድረሻ ሆኖ እንዲያገለግል ታስቦ የለማ መሠረተ-ልማት ነው፤

፴፮/ "**የሀገር ውስጥ የመንገድ ትራንስፖርት አገልግሎት**" ማለት ሁለት ወይም ከሁለት በላይ ክልሎችን በሚያገናኝ መንገድ ላይ የሚከናወን የንግድ መንገድ ትራንስፖርት አገልግሎት ነው፤

፴፯/ "**ክልል**" ማለት በሕገ መንግስቱ አንቀጽ ፵፯ መሠረት የተቋቋመ ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮችን ይጨምራል፤

፴፰/ "**ዓለም-አቀፍ የመንገድ ትራንስፖርት አገልግሎት**" ማለት የኢትዮጵያን ድንበር አቋርጦ የሚካሄድ ድንበር አቋራጭ የንግድ መንገድ ትራንስፖርት አገልግሎት ነው፤

፴፱/ "**ቢሮ**" ማለት የትራንስፖርት ሕጎችን ለማስፈጸም ሥልጣን የተሰጠው የክልል አስፈፃሚ አካል ነው፤

34/ "**Cargo Terminal**" means a hub infrastructure developed and designated for loading, unloading by cargo trucks; packing and unpacking of cargos by cargo transport operators;

35/ "**Warehouse**" means an infrastructure specifically designated for the purpose of departure or destination of cargo transport services;

36/ "**National Road Transport Services**" means a commercial transport service operated on roads connecting two or more Regions;

37/ "**Region**" means any Regional States established as per Article 47 of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia; and includes Addis Ababa and Dire Dawa City Administrations;

38/ "**International Road Transport Service**" means border crossing road transport service conducted by crossing the Ethiopian border;

39/ "**Bureau**" means a State Executive Organ in charge of enforcing road transport laws;

፵/ **“ልዩ ሥልጠና”** ማለት የጸና መደበኛ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ላለው አሽከርካሪ ለልዩ የአሽከርካሪ ባለሙያነት በሚኒስቴሩ ወይም በክልል ተለይቶ የሚሰጥ ሥልጠና ነው፤

፵፩/ **“መደበኛ ሥልጠና”** ማለት የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ለሌለው ሰው ለመጀመሪያ ጊዜ ወይም አስቀድሞ የያዘውን የአሽከርካሪነት ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ምድብ ለመቀየር ወይም ለማሳደግ የሚሰጥ ሥልጠና ነው፤

፵፪/ **"ሰው"** ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት ችሎታ የተሰጠው ነው፤

፵፫/ በዚህ አዋጅ ውስጥ በወንድ ጾታ የተገለጸው የሴት ጾታንም ያጠቃልላል፡፡

## ፫. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

ይህ አዋጅ ሁለትና ከሁለት በላይ ክልሎችን በሚያገናኙ ማናቸውም መንገዶች ላይ በሚከናወኑ የመንገድ የትራንስፖርት አገልግሎቶች፣ ኢትዮጵያን ከጎረቤት ሀገራት ጋር በሚያገናኙ ማናቸውም መንገዶች ላይ በሚሰጡ የመንገድ ትራንስፖርት አገልግሎቶችና መሠረተ-ልማቶች፣ እንዲሁም የኢትዮጵያ መንገዶች በሚገለገሉና በሚንቀሳቀሱ ሁሉም ተሽከርካሪዎች፣ አሽከርካሪዎች እና የመንገድ ተጠቃሚዎች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

40/ "**Special Training**" means training specially provided for holder of a valid regular driving permit as identified by the Ministry or Region for acquiring a special driving license;

41/ "**Regular Training**" means training given for the first time to persons with no driving permit; or to persons intending to change their existing valid driving permit to a different category; or to persons upgrading their valid driving permit;

42/ “**Person**” means any natural or juridical person;

43/ Any expression in the masculine gender includes the feminine.

## 3. <u>Scope of Application</u>

This Proclamation shall be applicable to all transport services carried out on all roads linking two or more Regions; to any road infrastructures and transport services carried out on such roads which link Ethiopia with neighboring Countries; and on all vehicles using roads in Ethiopia, on all drivers and all other road users.

**፬. የአዋጁ ዓላማዎች**

የአዋጁ ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው፤

፩/ አስተማማኝ፣ የተቀናጀ፣ ዘመናዊና ሁሉን አቀፍ የመንገድ ትራንስፖርት አገልግሎት ተደራሽነትን ማረጋገጥ፤

፪/ የመንገድ ትራንስፖርት አገልግሎት ደኅንነትን ማረጋገጥ፤

፫/ የመንገድ ትራንስፖርት አገልግሎት ከአካባቢ ብክለት የጸዳና ለአካባቢ ተስማሚ መሆኑን ማረጋገጥ፤

፬/ ቀጠናዊ የትራንስፖርት ትስስርን በማጠናከር ቀልጣፋ ዓለም ዓቀፍ የሎጂስቲክስ አፈጻጸም ውጤታማነትን ማጎልበት፤

፭/ ሀገር ዓቀፍ የትራንስፖርት አገልግሎት የተሳለጠና ተመጋጋቢ እንዲሆን ማድረግ፤

**ክፍል ሁለት**

**ስለሚኒስቴሩ ሥልጣንና ተግባር**

**፭. የሚኒስቴሩ ሥልጣንና ተግባር**

ሚኒስቴሩ በፌደራል አስፈጻሚ አካላት ሥልጣንና ተግባር መወሰኛ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፷፫/፪ሺ፲፬ የተሠጡት ሥልጣንና ተግባራት እንደተጠበቁ ሆነው በተለይ የመንገድ ትራንስፖርትን በተመለከተ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

**4. Objectives of the Proclamation**

The Proclamation has the following objectives:

1/ to ensure the accessibility of an reliable, integrated, modern and comprehensive road transport services;

2/ to ensure the safety of the road transport services;

3/ to ensure the road transport service is free from environmental pollution and environment friendly;

4/ to ensure a strong regional transport integration that enables an enhanced logistics performance;

5/ to ensure intermodal integration of the national transport services.

**PART TWO**

**POWER AND DUTIES OF THE MINISTRY**

**5. Power and Duties of the Ministry**

Without prejudice to the powers and duties vested in it by The Definitions of Powers and Duties of the Federal Executive Organs Proclamation No. 1263/2021, the Ministry shall, on road transports in particular, have the following powers and duties:

፩/ የመንገድ ትራንስፖርትን የሚመለከቱ የፖሊሲ ሐሳቦችንና ሕጎችን ያመነጫል፣ ሲጸድቁም ተግባራዊ ያደርጋል፤ አፈጻጸማቸውንም ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤

፪/ የመንገድ ትራንስፖርት አገልግሎት ደኅንነቱ የተረጋገጠ፣ ቀልጣፋ፣ አስተማማኝ፣ ፍትሃዊ እና ተደራሽ እንዲሆን ለማድረግ የሚያስችሉ ተግባራትን ያከናውናል፤ እንዲከናወኑ ያደርጋል፤ ያስተባብራል፤ ይቆጣጠራል፤

፫/ በአካል ጉዳተኝነት ምክንያት ልዩ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው የመንገድ ተጠቃሚዎች ምቹ የሆነ የመንገድ የትራንስፖርት አገልግሎት እንዲስፋፋ ያደርጋል፤ አተገባበሩ ላይ ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል፤

፬/ ኢትዮጵያ የተቀበለቻቸውን የመንገድ ትራንስፖርትን የሚመለከቱ ዓለም አቀፍ፤ አህጉራዊና ቀጣናዊ ስምምነቶች ተግባራዊነት በሀገር አቀፍ ደረጃ ይከታተላል፤

፭/ ሁለት እና ከሁለት በላይ የሆኑ ክልሎችን የሚያገናኙ አውራ ጎዳናዎች ላይ የሚከናወኑ የትራንስፖርት አገልግሎቶችን ያስተዳድራል፤ ይቆጣጠራል፤ የትራንስፖርት አገልግሎቶችን ተደራሽነት ያረጋግጣል፤

፮/ በኢትዮጵያ ውስጥ የተቀናጀ የሕዝብ ማመላለሻና የዕቃ ማጓጓዣ የመንገድ ትራንስፖርት አገልግሎት ሥርዓት እንዲስፋፋ፤ መንገደኞች፣ ዕቃዎችና ፖስታዎች በንግድ የመንገድ ትራንስፖርት ስለሚጓጓዙበት ሁኔታ የአሰራር መመሪያ ያወጣል አፈፃፀሙን ይከታተላል፤

1/ initiate policies and laws relating to road transport; and implement the same upon approval; follow up and supervise their implementations;

2/ undertake, cause to be undertaken, and supervises activities that ensure the safety, efficiency, reliability, fairness and accessibility of road transport services;

3/ ensure the availability of safe and suitable road transport service for people with special needs due to disability; monitor and inspect its implementation;

4/ follow up the implementation at national level of International, Continental or Regional Road Transport related Agreements to which Ethiopia is a Party;

5/ administer, supervise and ensure accessibility of road transport services carried out on high ways linking two or more regions;

6/ issue Directive for the development of an integrated passenger and cargo transport system throughout Ethiopia; the transportation of passengers, goods and postal services through commercial road transport; and follow up their implementation;

፯/ የንግድ የመንገድ ትራንስፖርት ሥራ ላይ በተሰማሩ ግለሰቦች እና ድርጅቶች የገበያ እጦት ሲያጋጥም ወይም ለተገልጋዩ ህብረተሰብ የመንገድ የትራንስፖርት አገልግሎት አቅርቦት እጥረት ሲከሰት ተገቢውን ክትትል በማድረግ የመፍትሄ እርምጃዎችን ተግባራዊ ያደርጋል፤ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም በገበያ ሥርዓት መሠረት አገልግሎት እንዲሰጡ ያደርጋል፤

፰/ በህዝብ ማመላለሻ ትራንስፖርት አገልግሎት ላይ የሚሰማሩ ግለሰቦች ወይም ድርጅቶች የሚያቀርቡለትን የስምሪት ፕሮግራም መርምሮ ያጸድቃል፤ የስምሪት ፕሮግራሙ ፍትሃዊነትና አተገባበር ላይ ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል፤ የስምሪት ፕሮግራም ካልቀረበለትም በራሱ አዘጋጅቶ ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል፤ ለዚሁ የወጣውን የዲሲፕሊን መመሪያ ይተገብራል፤

፱/ የተፈጥሮ አደጋ ሲያጋጥም ወይም ጊዜያዊ የኢኮኖሚ ወይም የማህበራዊ ችግሮች ሲከሰቱ ወይም ለሕዝብ ጥቅም አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ የንግድ የመንገድ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎችን በአስፈላጊው ቦታና መስመር በመደልደል እንዲሰማሩ ያደርጋል፤ ስምሪቱን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤

፲/ በሀገር ውስጥና ዓለም አቀፍ የንግድ የመንገድ ማመላለሻ ሥራ ላይ የተሰማሩ ግለሰቦች ወይም ድርጅቶች የሚያቋቁማቸውን የንግድ ተቋሞች የትራንስፖርት አሠራር የሚመለከት መመሪያ ያወጣል፤ ለእነዚህ ግለሰቦችና ድርጅቶች የሙያ ብቃት ደረጃ እና የኦፐሬተርነት ብቃት መስፈርት ይወስናል፤ የሙያ ብቃትና የኦፐሬተር ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ይሰጣል፤ ያድሳል፤ ይሰርዛል፤

7/ enforce appropriate remedial measures where individuals or enterprises engaged in commercial road transport may face demand deficit or where the public faces with supply side deficit of road transport services; and, where necessary, employ a market based approach;

8/ Approve trip schedules submitted to it by individuals or enterprises engaged in public transport services; follow up and supervise the fairness and implementation of approved trip schedules; develop schedules and implement where no such schedules are submitted to it; implement disciplinary Directive;

9/ mobilize and assign commercial road transport vehicles to operate in areas and routes where their service are demanded, where the occurrence of a natural disaster or sever economic reasons or social crises or public interest so demand; follow up and supervises the implementation of same;

10/ issue Directives governing the operation of the transport services of individuals or enterprises engaged in national and international commercial road transport services; determine levels and requirements for competence to be operators; issue, renew or cancel operators competence

ለድንበር አቋራጭ ተሽከርካሪዎች ፈቃድ ይሰጣል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

፲፩/ በሀገር ውስጥ የንግድ የመንገድ ማመላለሻ ሥራ ላይ የተሰማሩ ግለሰቦች ወይም ድርጅቶች የሚያስከፍሉትን ታሪፍ በተመለከተ ለሚሰጡት አገልግሎት ማግኘት ስለሚገባቸው ጥቅም እና የተጠቃሚዎችን የመክፈል አቅም በሚመለከት በየጊዜው ጥናት ያካሂዳል፣ የአገልግሎት ሰጪውንና የአገልግሎት ፈላጊውን ጥቅም እና አቅም ግምት ውስጥ በማስገባት የታሪፍ መጠኑን ሊወስን ይችላል፤

፲፪/ በዓለም አቀፍ የንግድ የመንገድ ትራንስፖርት አገልግሎት የሚስፋፋበትን ሁኔታ እያጠና ተግባራዊ ያደርጋል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

፲፫/ በዓለም አቀፍ የመንገድ ትራፊክ የሚሰማሩ ተሽከርካሪዎችንና አሽከርካሪዎችን አመዘጋገብ ሥርዓት ይወስናል፣ የአሽከርካሪዎችንና የተሽከርካሪዎቹን የምዝገባ ሰርተፊኬት ወይም ልዩ ፈቃድ ይሰጣል፣ ሌሎች የተሽከርካሪዎቹን መለያዎች ይወስናል፣ ፈቃድ ይሰጣል፣ ይቆጣጠራል፣ በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ ዓለም አቀፍ የመንገድ ትራፊክን ያስተዳድራል፤

፲፬/ ከመንገድ ትራንስፖርት አገልግሎት አሰጣጥ ጋር በተያያዘ በማንኛውም አካል መካከል አለመግባባትና ክርክር ሲፈጠር እና ባለጉዳዮቹ ሲጠይቁ በግልግል አይቶ ይወስናል፣ እንዲሁም በሁለት ወይም ከሁለት በላይ በሆኑ ክልሎች መካከል

permit; issue cross-border permits; follow up and supervise its implementation;

11/ undertake periodic review of tariff and may determine tariff cap on individuals or enterprises engaged in national commercial public transport services having due considerations to their services as well as the overwhelming economic capability of the consumer; and may determine tariff cap where the above circumstances demand so;

12/ study and implement mechanisms on the expansion of international commercial road transport services; and follow up and supervise its implementation;

13/ determine the registration system of drivers and vehicles engaged in international road traffic; issue registration certificate or special permits to these drivers and vehicles; decide on other vehicle identifications; issue licenses; supervises and administers international road traffic within the Ethiopian territory;

14/ provide arbitration services when so requested by adversaries engaged in commercial road transport services; and provide final administrative decisions on disputes involving two or more regions and relating to road

የትራንስፖርት አገልግሎትን አስመልክቶ አለመግባባት ቢፈጠር አለመግባባቱ ላይ የመጨረሻ አስተዳደራዊ ውሳኔ ይሰጣል አፈጻጸሙን ያረጋግጣል፤

፲፭/ በኢትዮጵያ ውስጥ የሞተር አልባ ትራንስፖርት ከሀገራችን ጂኦግራፊያዊ አቀማመጥ እና አየር ንብረት ጋር በሚጣጣምና ለተጠቃሚው በሚያመች መልኩ እንዲስፋፋ ያደርጋል፤ የማበረታቻ የአሰራር ሥርዓቶችን ይዘረጋል፤ አተገባበራቸውን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤

፲፮/ መንገዶችን የሚጠቀሙ ባለሞተር ተሽከርካሪዎች በሚሰጡት አገልግሎት ዓይነት ሊኖራቸው የሚገባውን ክብደትና መጠን እንዲሁም የተሳፋሪን ብዛትና የጭነት ክብደት ይወስናል፤

፲፯/ ከውጭ ሀገር የሚመጡትን፤ በሀገር ውስጥ የሚሠሩትንና የሚገጣጠሙትን ወይም በከፊል የሚሠሩትን ወይም በሥራ ላይ የተሰማሩ ማናቸውም ዓይነት ባለሞተር ተሽከርካሪዎች የዕድሜ ገደብ በማስወሰን ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤ ለዚሁም መመዘኛ የሚያገለግል ዝርዝር መስፈርት ያወጣል፤ ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል፤

፲፰/ የመንገድ ደህንነት ደረጃዎችን ያዘጋጃል፤ በእነዚህ ደረጃዎች መሠረት የተሽከርካሪዎችን አመዘጋገብና የቴክኒክ ምርመራ የሚመለከት መመሪያ ያወጣል ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤

transport services; and ensure its implementation;

15/ ensure the development of non-motorized transport services in Ethiopia as may be suitable to the users and harmonious with the geography and environment; implement incentive mechanisms; follow up and supervise its implementation;

16/ determine the weight and dimension, number of passengers and payload of motor vehicles depending on the transport services they are purposed for;

17/ follow up and implement decisions relating to vehicle age limit on imported, locally manufactured, assembled or semi-assembled motor vehicles or motor vehicles already in use; and issue technical specifications thereof; undertake monitoring and supervision;

18/ issue standards relating to road safety; issue Directives for the registration and inspection of vehicles; and monitor its proper enforcement;

፲፱/ ማናቸውንም የተሽከርካሪ ጋራዥ የቴክኒክ ብቃት ለማረጋገጥ፣ የሥራ ፈቃድና ዕድሳት አሰጣጥ እና ደረጃውን ለመወሰን የሚያስችል መመሪያ ያወጣል፤ የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ይሰጣል፤ ያድሳል፤ ይሰርዛል፤

፳/ ተሽከርካሪዎች እንደገና ስለሚሠሩበት፣ ስለሚፈቱበት ወይም ይዘታቸውንና አገልግሎታቸውን ስለሚቀይሩበት ሁኔታ; አገልግሎት የማይሰጡና ከጥቅም ውጭ የሆኑ ተሽከርካሪዎች ወይም በዕድሜ ገደብ ምክንያት አገልግሎት እንዳይሰጡ የሚደረጉ ተሽከርካሪዎች ስለሚወገዱበት ሁኔታ መመሪያና የአሰራር ሥርዓት በማውጣት ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤

፳፩/ የንግድ የመንገድ ትራንስፖርት አገልግሎት እንቅስቃሴን የሚመለከቱ መረጃዎችን በቴክኖሎጂ በተደገፈ አሠራር ይቆጣጠራል፣ መረጃ ያጠናቅራል ጥቅም ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፤

፳፪/ የባለሞተር ተሽከርካሪዎች ማቆሚያን፣ የሕዝብ ትራንስፖርት መናኸሪያዎችን፣ የአውቶቡሶች ዴፖን፣ የጭነት ተርሚናሎችን ደረጃዎች ይወስናል፣ አተገባበራቸውን ይከታተላል፣ እንደአስፈላጊነቱም እነዚህን የትራንስፖርት መሠረተ-ልማቶች ያስፋፋል፤ ያስተዳድራል፤

፳፫/ የባለሞተር ተሽከርካሪዎችን የቴክኒክ ምርመራ የሚያከናውኑ፤ የልዩ ማሽነሪ አሽከርካሪነትን ጨምሮ ልዩ ወይም መደበኛ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ሥልጠና የሚሰጡ ተቋማትን ደረጃ ይወስናል፤ ለእነኚህና ለአሽከርካሪ አሠልጣኞች የብቃት

19/ issue Directives under which certification of technical competence, operational license and levels of vehicle maintenance and overhaul garages may be determined, issue, renew, cancel certificate of competence;

20/ determine through Directives the manufacturing, dismantling, refurbishment or changing the original purpose of motor vehicles; scraping or disposing of motor vehicles either due to damage or vehicle age limit; follow up and supervise its implementation through guidelines developed for this purpose;

21/ monitor the movement of commercial road transport services through technology based platforms; consolidate data relating thereof and employ the data for appropriate purposes;

22/ determines standards to motor vehicle parking areas, public transport stations, cargo terminals, depots; ensure their observance; and where appropriate it shall develop and administer such infrastructures;

23/ determines, through Directives, standards for vehicle inspection and drivers training institutions including special or ordinary drivers permit drivers training institutions; issue, renew or cancel certificate of

ማረጋገጫ ፈቃድ ይሠጣል፤ ያድሳል፤ ይሰርዛል፤ የሚመለከታቸው አካላት የሚያከናውኑትን የብቃት ማረጋገጫና የሥራ ፈቃድ አሰጣጥ ይመረምራል፤ ይቆጣጠራል፤ አሰራራቸውን ይከታተላል፤

፳፬/ የተለያዩ ዓይነት ተሽከርካሪዎችን ለማሽከርከር የሚያስችሉ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫዎችን ደረጃ፣ ዲዛይን፣ ቀለም ዝርዝር ይዘታቸውን ይወስናል፤ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ለማግኘት የሚያስፈልጉ መስፈርቶችን ይወስናል፤ አፈጻጸማቸውን ይቆጣጠራል፤

፳፭/ በፌደራል ደረጃ ወይም በክልል ቢሮዎች በሚመዘገቡ ማናቸውም ዓይነት ተሽከርካሪዎች ላይ ለሚለጠፍ ሠሌዳ ዝርዝር መስፈርት ያወጣል፤ እንዲመረት ያደርጋል፣ ሥርጭቱንና አጠቃቀሙን ይከታተላል፣ አገልግሎታቸውን የጨረሱ ሠሌዳዎች የሚወገዱበትን እና ባለቤታቸው ጠፍቶ ብዙ ጊዜ የቆሙ ተሽከርካሪዎች የሚሰበሰቡበትንና የሚወገዱበትን ሁኔታ ይወስናል፤ አፈጻጸማቸው ላይ ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል፤ ሠሌዳ ለሌላቸው አዲስ ተሽከርካሪዎች ለአንድ ጊዜ ጉዞ ብቻ የሚያገለግል መሸኛ ይሰጣል፤

፳፮/ ተግባርና ኃላፊነቱን በአግባቡ ለመፈፀም እንዲቻለው ተቆጣጣሪዎችን በቋሚነትም ሆነ በጊዜያዊነት በማንኛውም የኢትዮጵያ ክልል ውስጥ ሊመድብ ይችላል፤

፳፯/ የመንገድ ትራንስፖርት ዘርፉንና የተጠቃሚውን ህብረተሰብ ደኅንነት በሚጎዳ ወይም አደጋ ላይ በሚጥል በማንኛውም አካል ላይ ተገቢው ሕጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል፤

competence for them; inspect, supervise the enforcement of same by other concerned organs; follow up their performance;

24/ determine through Directives the different classes of driving permits, the designs, colors and detailed contents; and requirements for getting such driving permits; and monitor and supervise their implementation;

25/ set standards through Directives and cause the manufacturing of plates for all categories of motor vehicles to be registered either at the federal or regional transport bureau; cause their production; follow up the distribution and proper usage; determines the situation to discard and dispose worn-out plates and vehicles abandoned with no claims; follow up and supervise their implementation; issues a single trip pass for new vehicles having no plates;

26/ assign supervisors on permanent or temporary basis in any region in Ethiopia for the proper execution of its duties and responsibilities;

27/ Cause legal measures to be taken against any body engaging in illegal acts that may harm the safety of the road transport sector and the public using it;

፳፰/ የመንገድ ትራንስፖርት አገልግሎቶች በአካባቢና አየር ንብረት የሚኖራቸውን ተፅዕኖ ለመቀነስ የሚያስችሉ ስልቶችን በመለየትና ከሌሎች አካላት ጋር በመተባበር በሥራ ላይ ያውላል፤ አተገባበራቸውን ይቆጣጠራል፤

፳፱/ በትራንስፖርት ዘርፍ የተሰማሩ ሰዎች፣ ድርጅቶች እንዲሁም የሚመለከታቸው የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች እና ተጠቃሚ ህብረተሰብ የሚወከሉበት አማካሪ ጉባዔ ያቋቁማል፤

፴/ የመንገድ ትራንስፖርት ዘርፉን ለማዘመን የመንገድ ትራንስፖርትን የሚመለከቱ ሀገር አቀፍ መረጃዎችን ለመሰብሰብ፣ ለማደራጀት እና ለማሰራጨት የሚያስችል የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ማዕከል ያደራጃል፤ የመረጃ ሥርጭት ሥርዓትን በመዘርጋት የሚመለከታቸው አካላት ጥቅም ላይ እንዲያውሉት ያደርጋል፤

፴፩/ የመንገድ ትራንስፖርት አገልግሎትን ለማቀላጠፍና ደህንነቱን ለመጠበቅ በተሽከርካሪዎች ላይ የሚገጠሙ ወይም በአሽከርካሪዎች የሚተገበሩ ቴክኖሎጂዎችና የመገናኛ ቁሳቁሶችን ደረጃ ከሚመለከተው አካላት ጋር በመተባበር ይወስናል፣ ይህን አገልግሎት ለሚሰጡ ተቋማት የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ይሰጣል፤ ያድሳል፤ ይሰርዛል፤ ተግባራዊነታቸውን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤

28/ identify and implement, in coordination with concerned organs, measures that mitigate the impact of road transport service on the environment and the climate; monitor its implimentation;

29/ establish an advisory council comprising of members represented from persons, enterprises engaged in the transport sector, the concerned government organs and the service users;

30/ organize information technology data center for the collection, consolidation and dissemination of data nationwide relating to the road transport services; and that enable to modernize the road transport services; put in place an information distribution system and ensure that relevant stakeholders utilize it;

31/ in collaboration with the concerned organs, issues standards of technologies and communications equipment that may be fixed to vehicles or operated by drivers for the efficient and safe road transport service; and issue, renew or cancel certificate of competence for institutons providing such services; follow up and supervise their implementation;

፴፪/ ዓለም ዓቀፍ የማኔጅመንት መስፈርቶችን ተጠቅሞ የትራንስፖርት ቢሮዎችን እና የመንገድ ትራንስፖርት አገልግሎት ሰጪዎችን የአፈጻጸም ደረጃ በየዓመቱ ይፋ ያደርጋል፤

፴፫/ በንግድ የመንገድ ማመላለሻ ሥራ ላይ የሚሰማሩ ወይም ንብረትነታቸው የዲፕሎማቲክ፣ የዓለም ዓቀፍ ድርጅቶች፣ ከአንድ ክልል በላይ የሚንቀሳቀሱ የተራድኦ ድርጅቶች ወይም የፌደራል መንግስት የሆኑ ባለሞተር ተሽከርካሪዎችን በራሱ ወይም ውክልና በሰጠው አካል መመዝገባቸውንና የቴክኒክ ምርመራ ማድረጋቸውን ይከታተላል፤ ቁጥጥር ያደርጋል፤

፴፬/ ዓለም አቀፍና የሀገር ውስጥ የንግድ የመንገድ ትራንስፖርት አገልግሎት መሥመሮች ላይ ፍትሃዊ የስምሪት አገልግሎት እና አቅርቦት መኖሩን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤

፴፭/ ኢትዮጵያ አባል በሆነችበት የሦስትዮሽ የትራንስፖርትና የትራንዚት ፋሲሊቴሽን ፕሮግራም ላይ ኢትዮጵያን ወክሎ ይሳተፋል፤ በፕሮግራሙ ውስጥ የተካተቱና ሚኒስቴሩን የሚመለከቱ ተግባራትን ያከናውናል፤ በሀገር ዓቀፍ ደረጃም አፈጻጸማቸውን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤

፴፮/ የገጠርና የከተማ መንገዶችን በሚያስተሳስሩ መንገዶች ላይ የንግድ የመንገድ ትራንስፖርት አገልግሎት እንዲስፋፋ ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፤

32/ identify and publicize annual performance ratings of transport bureaus and road transport service providers based on international rating standards;

33/ conduct or cause to be conducted by organs to which such duty is delegated, the registration and annual technical inspection to motor vehicles engaged in commercial road transport services or which are owned by diplomatic missions, international organizations, aid organizations operating in more than one region, or the Federal Government; follow up and supervise the registration and annual technical inspection thereof;

34/ follow up and supervise that international and national commercial road transport service routes are fairly distributed and available;

35/ represent Ethiopia in the Tripartite Transport and Transit Facilitation Program in which Ethiopia is a party; execute activities in the Program that are duties of the Ministry; follow up and supervise their national implementation at a national level;

36/ support and follow up the expansion of commercial road transport services on roads linking urban and rural areas;

፴፯/ ለልዩ አገልግሎት ተብለው የተሰሩ ወይም የተሻሻሉ ተሽከርካሪዎችን የሚመለከት ዝርዝር የቴክኒክ መስፈርት ያዘጋጃል፤ ይመዘግባል፤ ተሽከርካሪዎቹ ለተሰሩበት ወይም ለተሻሻሉበት ልዩ አገልግሎት ብቻ ስለማዋላቸው ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል፤

፴፰/ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የማበረታቻ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸውን በዘርፉ የተሰማሩ ግለሰቦች ድርጅቶችና ተቋማትን በመለየት ለሚመለከተው የመንግሥት አካል በማቅረብ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፤

፴፱/ ታዳሽ ኃይልን የሚጠቀሙ ተሽከርካሪዎች በኢትዮጵያ ውስጥ የሚስፋፉበትን መንገድ እያጠና ተግባራዊ ያደርጋል፤ ለታዳሽ ኃይም ተጠቃሚ ተሽከርካሪዎች አገልግሎት የሚሰጡ የመሠረተ-ልማት አገልግሎቶችን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት እንዲስፋፉ ያደርጋል፤

፵/ በማንኛውም ዓይነት ኃይል የሚንቀሳቀሱ አዲስ ተሽከርካሪዎችን ለሚያመርቱ፤ ሙሉ ለሙሉ ለሚገጣጥሙና በከፊል ለሚገጣጥሙ አምራቾችና ገጣጣሚዎች፤ አዲስ ተሽከርካሪ ወደ ሀገር ውስጥ ለሚያስመጡ አስመጪዎች የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ይሰጣል፤ ያድሳል፤ ይሰርዛል፤

፵፩/ በሀገራችን ውስጥ የባለሞተርና ሞተር አልባ ተሽከርካሪዎች ማምረቻና መገጣጠሚያ ኢንዱስትሪ እንዲስፋፋ እገዛ ያደርጋል፤ ለዚህ ኢንዱስትሪ መስፋፋት ምቹ ሁኔታዎች እንዲፈጠሩ የሚመለከታቸውን አካላት በማቀናጀት ያስተባብራል፤

37/ develop detail technical manual and register vehicles that are designed or repurposed for special purposes; monitor and supervise that such vehicles are employed only for the purpose they are designed or repurposed;

38/ identify, where necessary, individuals, enterprises and institutions engaged in the road transport service that deserve special assistance or incentive and submit to the government; and execute when approved;

39/ study and implement mechanisms through which vehicles using renewable energy could be more accessible in Ethiopia, in collaboration with concerned organs, ensure the development of charging infrastructures;

40/ issue, renew or cancel competency license to new vehicle manufacturers, manufacturers and assemblers of assembled and semi-assembled vehicles; importers of new vehicles using any type of energy;

41/ provide support to the industry of manufacturing and assembling of motorized and non-motorized vehicles in Ethiopia; coordinate the creation of suitable investment environment for such industry in collaboration with

ቴክኒካዊ ብቃታቸውን በሚመለከት ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል፡፡

## ክፍል ሦስት

## የንግድ የመንገድ ትራንስፖርት አገልግሎት

**፮. ንግድ ፈቃድ አስፈላጊ ስለመሆኑ**

፩/ በንግድ የመንገድ ትራንስፖርት አገልግሎት ሥራ ላይ ለመሠማራት የሚፈልግ ማንኛውም ሰው በቅድሚያ በሕግ ሥልጣን ከተሰጠው አካል የትራንስፖርት ንግድ ፈቃድ ማግኘት አለበት፤

፪/ በንግድ የመንገድ ትራንስፖርት አገልግሎት ለማከናወን ማንኛውም ሰው የኦፐሬተርነት የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ለማግኘት ማሟላት የሚገባው መስፈርት ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

## ክፍል አራት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**፯. የመረጃ ማዕከል ስለማቋቋም**

፩/ ሚኒስቴሩ በዚህ አዋጅ የተሰጡትን ሥልጣንና ተግባራት የሚመለከቱ መረጃዎችን ለመሰብሰብና ለማጠናቀር የመረጃ ማዕከል ያቋቁማል፤

፪/ የክልል ቢሮዎች፣ የፌዴራልና የክልል ፖሊስ አደረጃጀቶች፣ የንግድ የመንገድ ማመላለሻ ግለሰቦችና ድርጅቶች ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ከመንገድ ትራንስፖርት ጋር የተያያዘ አስፈላጊውን መረጃ በተዘረጋው

concerned organs; undertakes monitoring and inspections regarding their technical worthiness.

## PART THREE

## COMMERCIAL ROAD TRANSPORT SERVICE

**6. Business License Necessary**

1/ Any person intending to engage in commercial road transport services shall first secure a valid transport business license from a legally authorized organ;

2/ The requirements to obtain operator's permit by any person for undertaking a commercial road transport service shall be determined by a Directive to be issued by the Ministry.

## PART FOUR

## MISCELLANEOUS PROVISIONS

**7. Establishment of Data Center**

1/ The Ministry shall establish a data center to collect and compile the necessary information as regards its power and duties.

2/ The Regional Bureau, Federal and State Police Commissions, individuals or enterprises engaged in commercial road transport services shall have the duty to provide or transfer the

የቴክኖሎጂ መሠረተ-ልማት ለሚኒስቴሩ እና ለክልሉ ማቅረብ ወይም ማስተላለፍ ግዴታ አለባቸው፤

፫/ አስፈላጊውን መረጃ ለማስተላለፍ የሚረዳ የናሙና ቅፅ እና የቴክኖሎጅ መሠረተ ልማት ሚኒስቴሩ ያዘጋጃል፤ መረጃ የማስተላለፍ ግዴታ ላለባቸው አካላትም ያሰራጫል፡፡

## ፰. ስለ ሥልጣን ውክልና

፩/ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ሚኒስቴሩ ከሥልጣንና ተግባሩ በከፊል እንደ አግባቡ ለክልል የትራንስፖርት አስፈጻሚ አካላት እና ለሌሎች መንግስታዊ አካላት በውክልና ሊሰጥ ይችላል፡፡

፪/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ-አንቀጽ (፩) መሠረት ውክልና የተሰጣቸው አካላት በውክልና የተቀበሉትን ሥልጣንና ተግባር በሥራ ላይ ሲያውሉ ስለ መንገድ ትራንስፖርት የወጡ ሕጎችና ደረጃዎችን መከተልና ማክበር አለባቸው፡፡

## ፱. የተሻሩ፤ የተሰረዙና ፀንተው የሚቆዩ ሕጎች

፩/ የትራንስፖርት አዋጅ ቁጥር ፬፻፷፰/፲፱፻፺፯ በዚህ አዋጅ ተሽሯል፡፡

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) ድንጋጌ ቢኖርም በአዋጅ ቁጥር ፬፻፷፰/፲፱፻፺፯ መሠረት ወጥተው ወይም ፀንተው የነበሩ ደንቦች እና መመሪያዎች ሁሉ ከዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች ጋር እስካልተቃረኑ ድረስ በዚህ አዋጅ መሠረት እንደወጡ ተቆጥረው የፀኑ ይሆናሉ፡፡

necessary information relating to road transport through the technology infrastructure established for this purpose to the Ministry;

3/ The Ministry shall develop sample format and technology infrastructure necessary to provide or transfer of such information; and disseminate same to organs having the obligation to transfer the information.

## 8. Delegation of Powers

1/ The Ministry may, where necessary and as may be appropriate, delegate part of its powers and duties to Regional transport executive organs and other government organs.

2/ The organs referred to in Sub-Article (1) of this Article shall, in exercising the powers and duties delegated to them, be abide by and observe laws and standards relating to road transport.

## 9. Repealed, Cancelled and Effective Laws

1/ The Transport Proclamation No.468/2005 is hereby repealed by this Proclamation.

2/ Without prejudice to the provisions of Sub-Article (1) of this Article all Regulations and Directives issued based on Proclamation No. 468/2005 shall, in so far as they are not inconsistent with the provisions of this Proclamation, be deemed to have been issued under this Proclamation and shall remain in force.

፫/ የተሽከርካሪ መለያና መመዝገቢያ አዋጅ ቁጥር ፮፻፹፩/፪ሺ፪ አንቀጽ ፲፭ እና አባሪው በዚህ አዋጅ ተሰርዘዋል፤

፬/ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፸፬/፪ሺ፲፩ አንቀጽ ፯፣ ፲፪ እና አባሪው በዚህ አዋጅ ተሰርዘዋል፤

፭/ በተሽከርካሪ መለያና መመዝገቢያ አዋጅ ቁጥር ፮፻፹፩/፪ሺ፪ አንቀጽ ፲፭ እና አባሪው፤ እንዲሁም በአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፸፬/፪ሺ፲፩ አንቀጽ ፯፣ ፲፪ እና አባሪው ውስጥ ተደንግገው የነበሩትን ጉዳዮች በሚመለከት ሚኒስቴሩ ኢትዮጵያ የተቀበለቻቸውን ዓለም ዓቀፍ ስምምነቶች መሰረት አድርጎ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ተፈጻሚ ይሆናሉ፤

፮/ ይህን አዋጅ የሚቃረን ሌላ ማንኛውም አዋጅ፣ ደንብ እና መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ አዋጅ ውስጥ በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

## ፲. ስለመብትና ግዴታዎች መተላለፍ

፩/ የአዲስ አበባ ከተማ የትራንስፖርት ባለስልጣንና የድሬዳዋ ከተማ የትራንስፖርት ጽህፈት ቤት ተጠሪነታቸው ለየከተማ መስተዳድሮቻቸው ሆኖ እራሳቸውን ችለው ሥልጣን ባለው አካል ይደራጃሉ፡፡

፪/ በትራንስፖርት አዋጅ ቁጥር ፬፻፷፰/፲፱፻፺፯ መሠረት ተቋቁመው የነበሩት የአዲስ አበባ እና የድሬዳዋ የትራንስፖርት ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች መብቶችና ግዴታዎች በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) መሠረት ለሚደራጁት የትራንስፖርት ተቋማት

3/ Article 15 and the Annex of Vehicle Identification and Registration Proclamation No. 681/2010 is cancelled by this Proclamation;

4/ Article 7, 12 and the Annex of Drivers' Competence Certification Proclamation No. 1074/2019 is cancelled;

5/ Matters covered by Article 15 and the Annex of Vehicle Identification and Registration Proclamation No. 681/2010 and Article 7, 12 and the Annex of Drivers' Competence Certification Proclamation No. 1074/2019 shall be governed by Directives to be issued by the Ministry in accordance with the international agreements ratified by Ethiopia.

6/ Any Proclamation, Regulation and Directive or practice inconsistent with the provisions of this Proclamation shall have no effect on matters stated herein.

## 10. Transfer of Rights and Obligations

1/ The Addis Ababa Transport Bureau and the Dire Dawa Administration Transport bureau shall be established as independent bureaus of their respective city administrations through the appropriate organ;

2/ The rights and obligations of the Addis Ababa and Dire Dawa Transport Branch office established under Proclamation No. 468/2005 are hereby transferred to the respective transport bureaus to be established in accordance

ተላልፈዋል፡፡

## ፲፩. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

፩/ በትራንስፖርት አዋጅ ቁጥር ፬፻፷፰/፲፱፻፺፯ መሠረት የተቋቋሙና የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ የተሰጣቸው የንግድ የመንገድ ትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጡ ሰዎችና ድርጅቶች በዚህ አዋጅ እንደተቋቋሙና የብቃት ማረጋገጫው እንደተሰጣቸው ተቆጥረው ሥራቸውን ይቀጥላሉ፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው ድንጋጌ ቢኖርም በትራንስፖርት አዋጅ ቁጥር ፬፻፷፰/፲፱፻፺፯ መሠረት የተቋቋሙ ግለሰቦችና ድርጅቶች ይህ አዋጅ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ዕለት ጀምሮ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ በዚህ አዋጅ ሥልጣን በተሰጠው አካል እንደገና መመዝገብ አለባቸው፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፪) መሠረት ያልተመዘገቡ ግለሰቦች ወይም ድርጅቶች ተሰጥቶት የነበረው የኦፐሬተርነት ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ይሰረዛል፤ ዝርዝሩ ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፤

፬/ በትራንስፖርት አዋጅ ቁጥር ፬፻፷፰/፲፱፻፺፯ መሠረት ተመዝግበው የነበሩ የትራንስፖርት ማህበራት ይህ አዋጅ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ዕለት ጀምሮ ባሉት ዘጠኝ ወራት ውስጥ ወደ ንግድ ማህበርነት የመለወጥና አስፈላጊውን የኦፐሬተርነት የብቃት ማረጋገጫ ሥልጣን ካለው አካል የመውሰድ ግዴታ አለባቸው፡፡

with Sub-Article (1) of this Article.

## 11. Transitional Provisions

1/ Commercial Road Transport enterprises and individuals established or registered pursuant to Proclamation 468/2005 shall be considered as being established by this Proclamation and shall continue their activities.

2/ Notwithstanding the provisions of Sub-Article (1) of this Article, individuals and enterprises established as per Proclamation No. 468/2005 shall be re-registered within one year from the coming into force of this Proclamation;

3/ Persons or enterprises not re-registered in accordance with the provisions of Sub-Article (2) of this Article shall be revoked their operator's certificate; details shall be determined in the Directive to be issued by the Ministry;

4/ Commercial Road Transport Associations established pursuant to Transport Proclamation No. 468/2005 shall be re-established as a business company in accordance with the appropriate laws and secure their operators permit with nine months from the coming into force of this Proclamation;

፭/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፬) ከተጠቀሰው ጊዜ በኋላ ማንኛውም የትራንስፖርት ማህበር ምዝገባው እንደተሰረዘ ተቆጥሮ ምንም ዓይነት ሕጋዊ ሰውነት አይኖረውም፡፡

፮/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፬) መሠረት ወደ ንግድ ማህበርነት የሚለወጡ የቀድሞው የትራንስፖርት ባለሥልጣኑ ዘንድ ተመዝግበው የነበሩ ማህበራት ያፈሩትን ንብረት በሕግ አግባብ ወደሚለወጡበት የንግድ ማህበር ማስተላለፍ ይችላሉ፡፡

፯/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፮) የተደነገገው ቢኖርም በዚህ አንቀጽ መሠረት ወደ ንግድ ማህበርነት ሳይለወጥ የችሮታ ጊዜው ያለፈበት የትራንስፖርት ማህበር ያፈራው ንብረት ላይ አግባብነት ያለው የኢትዮጵያ የፍትሐብሔር ሕግ ድንጋጌ ተፈጻሚ ይደረጋል፡፡

፰/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፱ ንዑስ-አንቀጽ (፭) ስር የተደነገገው ተፈጻሚ እስከሚሆን ድረስ በተሽከርካሪ መለያና መመዝገቢያ አዋጅ ቁጥር ፮፻፹፩/፪ሺ፪ አንቀጽ ፲፭ እና አባሪው፣ እንዲሁም በአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፸፬/፪ሺ፲ አንቀጽ ፯፣ ፲፪ እና አባሪው ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል፣

5/ After the lapse of the period provided under Sub-Article (4) of this Article any Commercial Road Transport Association shall have considered dissolved and shall have no legal personality.

6/ Commercial Road Transport Associations registered in the former Authority and intending to re-establish as a commercial entity as per Sub-Article (4) of this Article may transfer they accumulated assets to the newly reestablished commercial entity.

7/ Without prejudice to the provisions of Sub-Article (6) of this Article, the accumulated assets of an Association which failed to be reestablished as a commercial entity shall be treated in accordance with the relevant provisions of the Ethiopian Civil Code.

8/ The provisions of Article 15 and the Annex of Vehicle Identification and Registration Proclamation No. 681/2010 and Article 7, 12 and the Annex of Drivers' Competence Certification Proclamation No. 1074/2019 shall continue to be applicable until such time that Sub-Article (5) of Article 9 of this Proclamation becomes effective.

**፲፪. ደንብ እና መመሪያ የማውጣት ስልጣን**

፩/ ይህን አዋጅ በአግባቡ ሥራ ላይ ለማዋል የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

፪/ ይህን አዋጅ እና አዋጁን መሠረት አድርገው የሚወጡ ደንቦችን በአግባቡ ሥራ ላይ ለማዋል ሚኒስቴሩ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

**፲፫. የመተባበር ግዴታ**

ማንኛውም አካል ለዚህ አዋጅ እና አዋጁን መሠረት አድርገው ለሚወጡ ደንቦች እና መመሪያዎች ተፈፃሚነት የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

**፲፬. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ዕለት ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሐምሌ ፰ ቀን ፪ሺ፲፬ ዓ.ም**

**ሣህለ ወርቅ ዘውዴ**
**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**12. Power to Issue Regulation and Directive**

1/ The Council of Ministers may issue Regulation for the proper implementation of this Proclamation.

2/ The Ministry may issue Directive necessarily for the proper implementation of this Proclamation and Regulations issued pursuant to this Proclamation.

**13. Duty to Cooperate**

Any person shall have the duty to cooperate for the implementation of this Proclamation, Regulations and Directives issued pursuant to this Proclamation.

**14. Effective Date**

This Proclamation shall enter into force from the date of its publication in the Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, On this 15th Day of July, 2022.**

**SAHLE-WORK ZEWDE**
**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**